

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



# በስኳር ኮርፖሬሽን የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን በተመለከተ



# የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ክፍል አንድ 1
መግቢያ ........................................ 1
የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት ራዕይ፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር ........................................ 3
ራዕይ ........................................ 3
ዓላማ ........................................ 4
ሥልጣንና ተግባር ........................................ 4
የስካር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ........................................ 5
የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት የፋይናንስ ምንጭ ........................................ 5
የኦዲቱ ዓላማ ........................................ 5
የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ........................................ 6
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) ........................................ 6
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) ........................................ 6
የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን ........................................ 7
የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description) ........................................ 7
ክፍል ሁለት 8
ግኝቶች ........................................ 8
የስኳር ልማት ፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ ........................................ 8
የፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ ........................................ 10
የፕሮጀክቶች የአዋጪነት ጥናትን በተመለከተ ........................................ 12
የፕሮጀክቶች የዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ ........................................ 13
የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ መኖሩን በተመለከተ ........................................ 16
የፕሮጀክቶቹ ስራ በውሉ በተጠቀሰው ዋጋ እና ጊዜ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ ........................................ 17
የፕሮጀክት ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ ........................................ 20
የፕሮጀክቶች ስራ በመንግስት የግዢ መመሪያ መሰረት በጨረታ መስጠቱን በተመለከተ ........................................ 22
የፕሮጀክቶች የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ ........................................ 23
ክፍል ሦስት 24
መደምደሚያ ........................................ 24
ክፍል አራት 27
የማሻሻያ ሃሳቦች ........................................ 27
አባሪ 1. የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ........................................ 30
አባሪ 2. የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የአሰራር ሥርዓት ትንተና (Process Description)……34
አባሪ 3. የአዳዲስ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ዕቅድ አፈጻጸም ........................................ 35

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ዘመናዊ የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ በግልና የውጭ ባለሃብቶችና በመንግስት ሽርክና በኩባንያ መልክ የተጀመረው በ1946 ዓ.ም ከአዲስ አበባ 110 ኪሎ ሜትር ዕርቃ ከምትገኘው ወንጂ ላይ ሲሆን በሽርክና ወደ ስራ የገባው ኤች.ቪ.ኤ የሚባል የደች ኩባንያ ነው፡፡ ኩባንያው አምስት ሺህ ሄክታር ሸንኮራ አገዳ ማልሚያ መሬት ተረክቦ ሰኔ 18 ቀን 1943 ዓ.ም ሥራ ጀመረ፡፡ ኩባንያው ግንባታውን መጋቢት 11ቀን 1946 ዓ.ም አጠናቆ ስኳር ማምረት ሲጀምር ፋብሪካው የነበረው ስኳር የመፍጨት አቅም በዓመት እስከ 70 ሺህ ቶን የሚደርስ ሲሆን ምዕዙን ስኳር እና ባለ አስር ሳንቲም እሽግ ስኳር ለገበያ ያቀርብ ነበር፡፡ በወቅቱ የወንጂ አካባቢ ለስኳር ምቹ የሆኑ አካባቢ ስለነበረ፡፡ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ምስረታ ጋር ተያይዞ በሰኔ ወር 1953 ዓ.ም የወንጂ ከረሜላ ፋብሪካ ተቋቁሞ ደስታ ከረሜላ አምርቶ ለገበያ ማቅረብ ጀመረ፡፡ በ1955 ዓ.ም እዛው ወንጂ ላይ የሸዋ ስኳር ፋብሪካ የተቋቋመ ሲሆን ፋብሪካው በወቅቱ በዓመት የነበረው ስኳር የመፍጨት አቅም ከ70 እስከ 80 ሺህ ቶን ድረስ ነበር፡፡
2. ለአገራችን ሁለተኛው የሆነው የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ በአክሲዮን መልክ ሰኔ 26 ቀን 1957 ዓ.ም በኢትዮጵያ መንግስትና የደች ኩባንያ በሆነው ኤች.ቪ.ኤ መካከል ተመስርቶ በ1962 ዓ.ም ልዮ ስሙ መርቲ በመባል በምትታወቅና ከአዲስ አበባ 200 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ ቦታ ፋብሪካው ተመርቆ ተከፈተ፡፡ መጀመሪያ ላይ ፋብሪካው ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚያውለው 11,000 ሄክታር መሬት ተሰጥቶት ወደ ምርት ሲገባ የማምረት አቅሙ በቀን 1,700 ኩንታል ስኳር ብቻ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ፋብሪካው አማካይ ዓመታዊ ስኳር የማምረት አቅም 1,300,000 ኩንታል ገደማ ነው፡፡
3. በ1967 ዓ.ም በተደረገው የመንግስት ለውጥ ፋብሪካዎቹ በመንግስት ይዞታ ስር እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ህግ ክፍል ማስታወቂ ቁጥር 58/1970 የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን እንዲቋቋም ተደርጎ ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካን፤ መተሃራ ስኳር ፋብሪካን፤ እንዲሁም አዲስ ከተማ እና አስመራ ከረሜላ ፋብሪካን እንዲያስተዳድር ተደርጓል፡፡ ኮርፖሬሽኑ በ1984 ዓ.ም በህግ ሲፈርስ በምትኩ በደንብ ቁጥር 88/85 መተሃራ ስኳር ፋብሪካ፣ ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና በደንብ ቁጥር 199/86 ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ (በወቅቱ አዲስ የተጀመረ የስኳር ልማት ፕሮጀክት ነበር) የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሆነው እንዲቋቋሙ ተደረገ፡፡
4. ለአገሪቱ ሶስተኛ ለሆነው የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ በ1967 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት ተካሂዶ የፊንጫ ሸለቆ ለስኳር ምርት አዋጭ ሆኖ ስለተገኘ፣ ጠለቅ ያለ ጥናት እንዲካሄድበት

ቡከርስ አግሪካልቸራል ኢንተርናሽናል ሊሚትድ በተባለ ኩባንያ አማካይነት ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ስለፕሮክቱ ዝርዝር ጥናት ተካሄደ፡፡ በፋይናንስ ዕጥረት ሳቢያ የተጓተተው የፋብሪካው ግንባታ ከአፍሪካ ልማት ባንክ፤ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ፣ ከአውስትራሊያ፤ ከስፔን መንግስት እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ባንኮች በተገኘ የፋይናንስ ምንጭ የፕሮጀክቱ የግንባታ ሂደት በጥር ወር 1981 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን የሸንኮራ አገዳ ተከላ ስራው የተጀመረው በ1984 ዓ.ም ነው፡፡ ከቀደምቶቹ ስኳር ፋብሪካዎች በተለየ ሁኔታ ዘመናዊ የሆነውን የዚህን የስኳር ልማት ፕሮጀክት የፋብሪካና ኤታኖል ግንባታ ያከናወኑት ኤፍ.ሲ.ሼፈርና አሶሽየትስ የተባለ አሜሪካ ኩባን እና በእርሱ ስር የፋብሪካውን ተከላ ያካሄደው ድዌቶ ኢንተርናሽናል የተባለ የደች ኩባንያ ሲሆኑ በርካታ የአገር በቀል ድርጅቶችም በግንባታው ተሳትፈዋል፡፡ የፋብሪካ ግንባታው የተጠናቀቀውም የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ኢሕአዴግ የደርግን ስርዓት በማስወገድ የተጀመረው የስኳር ልማት ስራ እንዲጠናቀቅ በወሰደው እርምጃ ነው፡፡

5. ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ግንባታው ተጠናቆ የሙከራ ምርት የጀመረው በየካቲት ወር 1990 ዓ.ም ቢሆንም መደበኛ ስራውን የጀመረው በ1991 ዓ.ም ሲሆን በዚሁ ዓመት ያስመዘገበው ዓመታዊ ምርት 500,000 ኩንታል ስኳር ነው፡፡
6. ይህ በእንዲህ እንዳለ ለስኳር ፋብሪካዎቹ የጋራ አገልግሎት እንዲሰጥ "የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል አክሲዮን ማህበር" በሶስቱ ስኳር ፋብሪካዎች፣ በልማት ባንክ እና በመድን ድርጅት አማካኝነት ህዳር 1990 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ በመቀጠልም አራተኛው በአፋር ብሔራዊ ክልል የተገነባው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በደንብ ቁጥር 122/98 ተመሰረተ፡፡ ይህ ፋብሪካ በ50 ሺ ሄክታር ላይ የሚለማ የሸንኮራ አገዳ መሬት እንዲኖረው እና ዓመታዊ የስኳር ምርት መጠኑ 619,000 ቶን እንዲሁም ዓመታዊ ኤታኖል ምርቱ 55.4 ሚሊዮን ሊትር እንዲሆን ታቅዶ ግንባታው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከዚህ በኃላ የኢትዮጲያ ስኳር ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከልን በማፍረስ የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 504/98 ተቋቋሞ የስኳር ፋብሪካዎቹን በመቆጣጠር፣ በፕሮጀክት ልማት፣ በምርምር፣ በስልጠናና በግብይት ረገድ ድጋፍ ሲሰጥ ቆየ፡፡
7. ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የኢትዮጵያ ስኳር ኤጀንሲ እንዲፈርስ ተደርጎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 የአሁኑ ስኳር ኮርፖሬሽን ተቋቋመ፡፡ ኮርፖሬሽኑ የስኳር ልማትን በአገራችን በስፋት ለማካሄድ በሚያስችለው መልኩ ተደራጅቶ በተግባር እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
8. መንግስት በነደፈው የአምስት ዓመት ዕቅድ መሰረት የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንደስትሪዎች ከመቼውም ጊዜ የላቀ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲስፋፉ፣ የአገራችን የስኳር ፋብሪካዎችም

የሚያመርቱት የስኳር ምርት እያደገ የመጣውን የአገር ውስጥ ፍላጎት ማርካት ባለመቻሉ ይህንኑ ዕጥረት ለመቅረፍ መንግስት ከፍተኛ ድጎማ እያደረገ ስኳር ከውጪ አገር አስገብቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ የሚያቀርብ በመሆኑ ይህንን የገቢ ምርት የሚተኩ የስኳር ፋብሪካዎችን በስፋት ለመገንባት በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ለስኳር ልማት ዘርፍ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

9. በኢንደስትሪ ልማት ስትራተጂው መሰረት ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በተለይ በአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ስር የሚመደበው የስኳር ልማት ንዑስ ዘርፍ በልማት ጥረት ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ነው፡፡ በስትራተጂው ለዚህ ዘርፍ ትኩረት የተሰጠው በብዙዎቹ ቆላማ የአገራችን አካባቢዎች ምርቱን ማምረት የሚቻል በመሆኑ፣ ለመስኖ ልማት የተመቹና የለማ ሰፊ መሬት በመኖሩ፣የአገር ውስጥ የስኳር ፍላጎት እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ፣ ለስኳር ምርት ሰፊ የውጭ ገበያ በመኖሩ፣ በመንግስት ፋብሪካዎች በኢንዱስትሪው ልማት ግንባር ቀደም ሚና እዲጫወቱ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ እና ፋብሪካዎቹን በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሁም በአውሮፓ ገበያ ለስኳር አምራች የአፍሪካ አገሮች የተሰጠውን ልዮ ዕድል መጠቀም የሚቻል በመሆኑ ነው፡፡

10. የስኳር ኮርፖሬሽን በስኳር ልማት ዘርፍ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አሁን ባሉት ሦስት ነባር ፋብሪካዎች በዓመት እየተመረተ ያለውን 300 ሺህ ቶን ገደማ የሚሆን ስኳር የማምረት አቅም ወደ 2.25 ሚሊዮን ቶን፣ 18 ሚሊዮን ሊትር የሚጠጋ ኤታኖል የምርት አቅም ወደ 181,604 ሜትር ኩብ፣ ከስኳር ተረፈ ምርት በዓመት ሊመረት የሚችለውን የኤሌክትሪክ ኃይል 101 ሜጋ ዋት ለማድረስ በትጋት እየሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ በነባሮቹና አዲስ በሚገነቡ የስኳር ፋብሪካዎች ፕሮጀክቶች 1,374,646 ሜትር ኩብ ኬሮሲን በማምረትና በዚሁ መጠን ከውጭ የሚገባውን ኬሮሲን በመተካት ለምግብ ማብሰያና ለሌሎች ግብዓቶች አገልግሎት ለማዋል እንዲሁም 44,340 ሜትር ኩብ ኤታኖል ለመቀየጫ (Blending) እንዲውልና አገራችን ለዚህ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለመቀነስ አቅዶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት ራዕይ፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር

### ራዕይ

11. በቀጣይ ዕድገት ላይ የተመሰረተና በዓለም ተወዳዳሪ የሆነ የስኳር ኢንደስትሪ መፍጠር፡፡

## ዓላማ

12. የኮርፖሬሽኑ ዓላማ የሀገሪቱን የስኳር ፍላጎት አቅርቦት ማረጋገጥ፣ በሀገሪቱ የስኳር ተጓዳኝ ምርቶችን በማሳደግ የኃይል አቅርቦትን መደገፍና ቁልፍ የኤኮኖሚ አገልግሎት ላላቸዉ ተግባራት ማዋል፣ የስኳር ንዑስ ሴክተር ለብሔራዊ ኤኮኖሚ ዕድገት የሚኖረውን አስተዋፅኦ ማሣደግ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ በዓለም ገበያ ከፍተኛ የኤክስፖርት ድርሻ መያዝ፣ የስኳር ልማት ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍን ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች ለመፈጸም የሚያስችል፣ የሰው ኃይል ልማት እና የምርምርና የቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚያደርግ ተቋማዊ ብቃት መፍጠር ነው።

## ሥልጣንና ተግባር

13. የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባሮች አሉት፡-

- የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ሌሎች ሰብሎችን ማልማት፤
- ስኳር፤ የስኳር ውጤቶችን እና የስኳር ተረፈ ምርት ውጤቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፤
- ምርቶቹንና ተረፈ ምርቶቹን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤
- አዳዲስና የማስፋፊያ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ የተከላና ኮሚሽኒንግ ስራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሸንኮራ አገዳና በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ውጤቶችን በስራ ላይ ማዋል፤
- አቅሙ ካለቸው የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግስት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፋብሬኬሽን ስራዎች በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤
- በሕግ መሰረት ለስራው የሚያስፈልገው መሬት ባለይዞታ መሆንና ማልማት፤
- የአገዳ ምርታቸውን ለመንግስት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያቀርቡ አገዳ አብቃዮችን ማበረታትና መደገፍ፤
- ለስኳር ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈልገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትምህርት ተቋማት ጋር መተባበር፤
- የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪና የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዘማጅ ስራዎችን መስራት፣

  የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፤

## የስካር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

14. የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት ሆኖ በአንድ ዋና ዳይሬክተር ሥር በ5 ወሳኝ የስራ ሂደቶች በ12 ደጋፊ የስራ ሂደቶች በድምሩ 17 የሥራ ሂደቶች ተዋቅረዋል፡፡ ዋና ዳይሬክተሩ አጠቃላይ በፖሊሲና እስትራቴጂክ አካሄድ ላይ ተመስርቶ በበላይነት የመምራትና የማቀናጀት የማስተባበር የመቆጣጠር ተግባር ይዞ ለሁሉም የስራ ሂደት ባለቤቶች ሙሉ የሥልጣን ውክልና በመስጠት ሥራውን በማከናውን ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለእነዚህ የሥራ ሒደቶች በመሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናት (BPR) መሠረት የሚያስፈልገው የሰው ሀይል ብዛት 321 ሲሆን በስራ ላይ ያለ የሰው ሀይል ግን 262 ነው፡፡ ይህም በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ሁለተኛ በድግሪ 39፤ መጀመሪያ ድግሪ 115፤ ዲፕሎማ 46፤ ሰርተፍኬት 4፤ ከ 9 -12ኛ ክፍል 31፤ ከ1-8 ክፍል 2 ሲሆን የ25 ሰራተኞች በሹመት እና በምደባ ኮርፖሬሽኑን የተቀላቀሉ በመሆናቸው የግል መህደራቸው አብሮ ባለመላኩ ምክንያት የትምህርት ደረጃቸውን ለማወቅ አልታቻለም፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት የፋይናንስ ምንጭ

15. የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ምንጭ ከስኳር ልማት ፈንድ፤ ከአገር ውስጥ ባንክ፤ ከሕንድ "EXIM" ባንክ እና ከቻይና ልማት ባንክ ብድር ሲሆን የፋብሪካዎች ኦፕሬሽን በጀት በዋነኛነት የሚሸፈነው ከስኳር ሽያጭ እና ከልዩ ልዩ ገቢ ነው፡፡ የዋናው መ/ቤት የሥራ ማስኬጃ በጀት ደግሞ ከፋብሪካዎች የስኳር ሽያጪ ድርሻ ላይ ከሚታሰብ 2.59 በመቶ የሽያጭ አገልግሎት ገቢ እና ቀሪው (ልዩነቱ) ደግሞ ከስኳር ልማት ፈንድ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በ2003፣ 2004 እና 2005 በጀት ዓመታት እንደየቅደምተከተሉ የተመደበለት በጀት ብር 7,630,103,806.93፤ 12,638,567,000 እና ብር 11,482,000,000.00 ቢሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ2003 በጀት ዓመት ብር 7,121,828,135.00፤ በ2004 በጀት ዓመት ብር 10,697,628,000.00 እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 9,162,000,000.00 ስራ ላይ አውሏል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

16. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ አፈጻጸምን በቁጠባ፤ በብቃት እና በስኬታማነት ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፤ በዚህ ዙሪያ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን

ወይም የአሰራር ግድፈቶችን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

17. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የስኳር ኮርፖሬሽን የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የግንባታ ሥራ ኢኮኖሚ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም የሚል ነው"፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue)

18. ከላይ በተገለጸው የኢዲት አካባቢ ሥር አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ተመርጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የመስኖ፣ ቤቶችና መሰረተ ልማት ግንባታን በቁጠባ፤ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል  የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፤
2. የአገዳ ተክል ልማት ተግባርን በቁጠባ፤ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል  የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፤
3. የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጅክት ተግባርን በቁጠባ፤ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል  የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፤
4. የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን የክትትል፤ የግምገማ፤ የድጋፍ ሥራ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም ከባለድርሻ አካለት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ  በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

19. ከላይ የተመረጡት አራት የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues) ለመመዘን የሚያስችሉ 41 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑ የኮርፖሬሽኑ መቋቋሚያ አዋጅ፣ ስትራቴጂክ ዕቅዶች፣ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ የሥራ መመሪያ እና በኮርፖሬሽኑ የተጠናው መሰረታዊ የስራ ሒደት ለውጥ ጥናቶች፣ መልካም ተሞክሮዎች፣ የሥራ አመራር ቃለ ጉባኤዎች እና የዳሬክተሮች ቦርድ ቃለ ጉባኤዎችን ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) **በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡**

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን

20. ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003 የበጀት ዓመት እስከ 2005 በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የሥራ ክንውን እና ፕሮጀክቶቹ ከተጀመሩ ጊዜ ጀምሮ ያሉ ጉልህ ጉዳዮች ነው፡፡ ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በስኳር ኮርፖሬሽን ዋና መስሪያ ቤት እና በናሙና በተመረጡ ሁለት ፕሮጀክቶች የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የማስፋፊያ ፕሮጀክት እና የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ሲሆን፣ ዋነኛ ባለድርሻ ከሆኑ አካላት የፋብሪካ ግንባታ የሥራ ሂደት፤ የሸንኮራ አገዳ ልማት የሥራ ሂደት፤ የመስኖ ግንባታና መሰረተ ልማት፤ ካሳ ክፍያ፤ መልሶ ማቋቋምና መሬት ርክክብ ዳይክቶሬቶች እንዲሁም የፕሮጀክቶችን ስራ ተቋራጮች፤ አማካሪ መሃንዲሶች እና የክልል መስተዳድር አካላትን በኦዲቱ ተካተው ታይተዋል፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ

21. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ቃለ-ምልልስ በማድረግ፣የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ ሲሆን በተጨማሪም ኦዲቱ በወንጂ ሸዋ ስኳር ልማት የማስፋፊያ ፕሮጀክት እና በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን በአካል በመገኘት ለየፕሮጀክቱ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪ መሃንዲሶች እና ባለድርሻ አካላት መጠይቅ በማድረግ እና የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

22. መንግስት ያስቀመጠውን GTP ዕቅድ በአለም አቀፍ ተወዳዳሪ የስኳር ኢንዱስትሪ መፍጠር፤ ለስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክቶች መሪ፤ ስትራተጂክና አመታዊ እቅድ ማዘጋጀት፤ ለፕሮጀክቶቹ የአዋጭነት፤የዲዛይን ጥናት እና የቴክኖሎጂ መረጣ ማከናወን፤ የአማካሪና የስራ ተቋራጮች መረጣና የውል ስምምነት ማፈራም፤ የመስኖና የመሠረተ ልማት ግንባታ ማከናወን፤ የመሬት ዝግጅትና የአገዳ ተከላ ትግበራ ማከሄድ፤ ለፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት የሲቪል ግንባታና የማሽነሪ ተከላ ስራዎችን ማከናወን፤ የኮሚሽኒንግና ርክክብ ሥራ ማከናወን፤ ስኳር ማምረት እና ለገበያ በማቅረብ በአለም አቀፍ ተወዳዳሪ የስኳር ኢንዱስትሪ መፍጠር ነው፡፡ ስዕላዊ መግለጫ (Process Description) **በአባሪ 2 ይመልከቱ፡፡**

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## የስኳር ልማት ፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ

23. ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች (አገዳ ተክል ልማት፣ ፋብሪካ ግንባታ እና የመስኖ ልማት) አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳይ መሪ ዕቅድ (Master plan) በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

24. በስኳር ኮርፖሬሽን የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት ደረጃውን የጠበቀና ከ4 ጊዜ በላይ ሊከለስ የማይችል የስኳር ኢንዱስትሪ መሪ ዕቅድ በ90 ቀናት፣ ደረጃውን የጠበቀና ከሁለት ጊዜ በላይ ሊከለስ የማይችል የተሟላ የስኳር ኢንዱስትሪ ስትራቴጂክ ዕቅድ በ90 ቀናት እና ደረጃውን የጠበቀና ከ2 ጊዜ በላይ ሊከለስ የማይችል የኦፐሬሽን ዕቅድና በጀት በ60 ቀናት ማዘጋጀት እንዳለበት ተገልጻል፡፡

25. ኮርፖሬሽኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት የስኳር ኢንዱስትሪ መሪ ዕቅድ (Master plan) ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡ መንግስት በነደፈውን የአምስት ዓመት ዕቅድ መሰረት የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንደስትሪዎች ከመቼውም ጊዜ የላቀ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲስፋፉና ያሉት የስኳር ፋብሪካዎችም የሚያመርቱት የስኳር ምርት እያደገ የመጣውን የአገር ውስጥ ፍላጎት ማርካት ባለመቻሉ ይህንኑ ዕጥረቱን ለመቅረፍ እና የገቢ ምርቱን የሚተኩ የስኳር ፋብሪካዎችን በስፋት ለመገንባት የሚያስችል በኮርፖሬሽኑ (አገዳ ተክል ልማት፣ ፋብሪካ ግንባታ እና የመስኖ ልማት) የሚያሳይ የአምስት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

26. በኮርፖሬሽኑ የአምስት ዓመታት ዕቅድ (2003-2007 ዓ.ም) መሠረት አዲስ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች የአገዳ ተክል ልማት ዕቅድ ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም በጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት 18,400 ሄክታር ሲሆን ክንውን 2,395 ሄክታር (13%)፤ በኦሞ ኩራዝ ዕቅድ 43,108 ሄክታር ሲሆን ክንውን 1,676.6 ሄክታር (4%) እና በወልቃይት እቅድ 8,608 ሄክታር ሲሆን ክንውን 539 ሄክታር (6.5%) መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

27. የፋብሪካ ግንባታ በአምስት ዓመታት ዕቅዱ መሠረት (ከ2003 - 2005 ዓ.ም) የፋብሪካ ግንባታው የጣና በለስ ቁጥር አንድ እና ሁለት እስከ ጥቅምት 2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ክንውኑ በ2005 ዓ.ም መጨረሻ ቁጥር አንድ 45% እና ቁጥር ሁለት 39% መሆኑ፣ በኦሞ-ኩራዝ የፋብሪካ ግንባታው እስከ ሰኔ 2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ክንውን 42% መሆኑ፤

ወልቃይት እስከ ጥቅምት 2006 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ሥራው ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመጀመሩ ታውቋል፡፡

28. የጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ እና ሌሎችም አዳዲስ ፕሮጀክት የአገዳ፣ የመስኖ እና የፋብሪካ ግንባታ ዕቅድ በኮርፖሬሽን ደረጃ ተዘጋጅቶ ለፕሮጀክቶቹ የሚላክ ሲሆን የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካላት ሊተገበሩት የሚገቡ ዝርዝር ሥራዎች በዕቅዱ ተካተው አለመዘጋጀቱ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

29. ይህንን በተመለከተ የጣና በለስ አገዳ ተክል ልማት እና የመስኖ ልማት የፕሮጀክት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአገዳ፣ የመስኖ እና የፋብሪካ ግንባታ ዕቅድ በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት በኩል የሚዘጋጅ መሆኑ፣ የፕሮጀክቶችን ስፋት፣ ያለውን የሰው ኃይል እና ሃብት ሳያገናዝብ የሚዘጋጅ እና ወደ ስራ የሚገባ በመሆኑ ዕቅዱን ለማሳካት አዳጋች እንዳደረገው ገልጸዋል፡፡

30. ከዚህም በተጨማሪ ኮርፖሬሽኑ ሊያከናወን ያቀዳቸው ፕሮጀክቶች ግባቸውን እንዲመቱ ሥራውን የሚተገብሩት አካላት በዕቅድ ዝግጅት ወቅት የማያሳትፍና ዕቅድ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት ዓመታዊ ዕቅዶች በዓመት ከሦስት ጊዜ በላይ የሚከለሱ መሆናቸውን እና የፕሮጀክቶቹ ዕቅድ አፈጻጸም በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ኮርፖሬሽኑን ተገቢ ላልሆነ ወጪ እየዳረገው ይገኛል፡፡

31. ከዚህ ጋር በተያያዘ በተንዳሆ ስኳር ፕሮጀክት የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት በታቀደለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት 5164.09 ሄክታር መሬት የለማ የሸንኮራ አገዳ ምርት ዕድሜው በመራዘሙ ምክንያት እንዲወገድ በመደረጉ 102,440,145.00 ብር ፋብሪካው ማግኘት የሚገባውን ገቢ ተገቢ ባልሆነ መልኩ ታጥቷል፡፡

32. ይህ የሚያሳየው እቅዱ አግባብ ባለው ጥናት ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ እና ኮርፖሬሽኑ ለፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም አስፈላጊውን ዝግጅት፤ የተጠናከረ የፕሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር አለመድረጉን እና የፕሮጀክቶቹ ኮንትራት አስተዳደር ጠንካራ አለመሆኑን ነው፡፡ ይህም ኮርፖሬሽኑ በአምስት ዓመታቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት በስኳር ልማቱ ዘርፍ የተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## የፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ

33.የአገዳ ተክል ልማት፣ የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት ተግባሪዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

34.ኮርፖሬሽኑ የሚያስገነባቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራን በተመለከተ ሪፖርት በየወሩ ሊቀርብና በሪፖርቱ መሰረት ግምገማ ሊከናውን ይገባል፡፡ የሚቀርበውም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የእያንዳንዱ ፕሮጀክት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ተለይቶ በዝርዝርና ግልጽ በሆነ መልኩ ሊያሳይ ይገባል፡፡

35. ከ2003 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም የቀረበው የአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች (ጣና በለስና ኦሞ ኩራዝ) የአፈጻጸም ሪፖርት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸሙን ለየብቻ በዕቅድ ከተያዘው ጋር በማነጻጸር በወሩ፣ በዓመቱ እና ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ምን ያህል እንደሆነ በልኬት እና በፐርሰንት የማይገለጽ መሆኑ ተዘጋጅቶ ከተላከው ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

36.ዕቅድ ክትትል ሪፖርትን በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትል የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፕሮጀክቶች ግምገማ በየወሩና በዓመት በአካል በመገኘት የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻጸሙ ላይ ውይይት የሚደረግ መሆኑን፣ሆኖም ግምገማው በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን ለወደፊቱ በተጨባጭ ግብረ መልሱን በማስረጃ በመታገዝ ለማከናወን እንደታቀደ ገልፀዋል፡፡

37.ኮርፖሬሽኑ በተጨባጭ የሚያከናውናቸው የፕሮጀክት ስራዎች የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻጸም በሪፖርት አለመካተቱ ፕሮጀክቶቹ በትክክል ምን ያህል ገንዘብ ወጪ እንደተደረገባቸው በውል ለመለየት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

38.ኮርፖሬሽኑ ባጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት የፕሮጀክቶች ዕቅድ ክንውን አፈፃፀም ልዩነት ከ10% በታች ማድረስ የሚል ቢቀመጥም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ዶመንቶች የዕቅድ አፈጻጸሙ  እንደሚከተለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

39. የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የአገዳ ተክል ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት አለመጠናቀቃቸው፣ይህም በ2004 ዓ.ም 2000 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ አፈጻጸሙ 490 ሄክታር (25%) ሲሆን፣ በ2005 ዓ.ም የዘር አገዳ 800 ሄክታር  እና የኮሜርሻል አገዳ 6200 ሄክታር ታቅዶ ክንውኑ የዘር አገዳ (ቲሹ ካልቸር) 626.8 ሄክታር (78%)፣ የኮሜርሻል አገዳ 1123.92 ሄክታር (18%) በድምሩ 1750.72 ሄክታር የዕቅዱን (25%) ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡

40.በወንጂ/ሸዋ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የአገዳ ተክል ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት አለመጠናቀቁ፣ ይህም በ2004 ዓ.ም 3288 ሄክታር ታቅዶ ክንውኑ 1540 ሄክታር (47%) ብቻ መሆኑ፣ በ2005 ዓ.ም 3000 ሄክታር ታቅዶ ክንውኑ በኡላጋ ሳይት 120 ሄክታር፣ በጠዴቻ

ሳይት 240 ሄክታር፣ በወሌንሶ ሳይት 270 ሄክታር፤በወለንጪቲ ሳይት 20 ሄክታር በድምሩ 650 ሄክታር (22%) ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡

41. የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የመስኖ ልማት በ2004 ዓ.ም 3750 ሄክታር ታቅዶ አፈፃፀሙ 412 ሄክታር (0.3%) ሲሆን በ2005 ዓ.ም ደግሞ የ10,000 ሄክታር (Sprinkler Irrigation) መስኖ ዘዴ እስከ 4ኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ለማጠናቀቅ ታቅዶ በምዕራፍ አንድ ከተያዘው 1,366 ሄክታር (13.7%) ተገንብቶ በፍተሻ ላይ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

42. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ማስፋፊያ ፕሮጀክት በ2005 ዓ.ም ውስጥ በጠዴቻ 300 ሄክታር፣ በወሌንሱ 600 ሄክታር፣ በወለንጪቲ 1510 ሄክታር፤በቦፋ 1710 ሄክታር በጠቅላላው 4120 ሄክተር የስፕሪንክለር የመስኖ መሰረተ ልማት ያለቀለት መሬት ለመረከብ ታቅዶ ክንውኑ በጠዴቻ 240 ሄክታር፣ በወሌንሶ 300 ሄክታር፣ በኡላጋ 120 ሄክታር፤ በወለንጪቲ 20 ሄክታር በድምሩ 680 ሄክታር (16.5%) ብቻ ሰርፌስ ኢሪጌሽን የተከናወነ መሆኑ ከቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. የጣና በለስ ቁጥር 1፤ ቁጥር 2 እና ኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት ስራቸው ከተጀመረ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2005 ዓ.ም ድረስ የሲቪል ወርክ፣ የኤሌክትሮ መካኒካል ኢሬክሽንና ኢንስታሌሽን ሥራዎች በማጠናቀቅ ለፍተሽ እና ለርክክብ ለማዘጋጀት የታቀደ ቢሆንም በኦዲት ወቅት ዝግጅት፤ ዲዛይን፤ የፋብሪካ ማሺነሪ ማምረት ማቅረብ፤ የሲቪል ሥራዎች ብቻ የተሠራ መሆኑ እና አፈጻጸሙም እንደየቅደም ተከተላቸው 45%፤ 39% እና 42% ብቻ መሆኑን ከቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርትና በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩን **በአባሪ 3 ተመልክቷል**)



ፎቶ 1. በጣና በለስ ቁጥር 1 የሲቪል ሥራው ብቻ እየተገነባ ያለው የፋብሪካ ግንባታ በከፊል

44. ከዚህም በተጨማሪ በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት በ2003 በበጀት ዓመቱ በነበረው የመስኖ ልማት መጓተት ምክንያት  ቀድሞ 2,000 ሄክታር ልማትና ተከላ ለማከናወን ታቅዶ የነበረው ተከላውን በመስኖ መጓተት መትከል እንደማይቻል ታምኖበት ዕቅዱ ወደ 230 ሄክታር ዝቅ ቢደረግም በተጨባጭ መትከል የተቻለው ግን 86 ሄክታር መሆኑ ታውቋል፡፡

45.እንዲሁም በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የወለንጪቲ ቦፋ የመስኖ ግንባታ ማስፋፊያ ፕሮጀክት በ2005 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ የተያዘ ቢሆንም የፕሮጀክቱ መሰረተ ልማት ዝርጋታውን ለአገዳ ተከላ ኮንትራክተሩ አጠናቆ ስላላስረከበ የእርሻና የአገዳ ተከላ ዕቅድን ማሟላት አለመቻሉ ታውቋል፡፡

46.የኮርፖሬሽኑ ጣና በለስ እና የወንጂ/ሸዋ የአገዳ ተክል ልማት እና የመስኖ ልማትና የፋብሪካ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለዕቅዶቹ አለመሳካት ዋነኞቹ ምክንያቶች በቅንጅት ያለማቀድ፤ ዋናው ኮንትራክተሩ እና ንዑስ ተቋራጮች ስራውን በዕቅድ ያለመምራታቸውና ክትትል እና ቁጥጥር ባለማድረጋቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

47.ከዚህም በተጨማሪ ከአገዳ ተክል ልማት፤ ከመስኖ ግንባታ እና ከፋብሪካ ግንባታ ክፍል ጋር የተቀናጀ እና የተጠናከረ የፕሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት በየዓመቱ ተደጋጋሚ የዕቅድ ክለሳ በማድረግ፤ የዕቅድ አፈጻጸም መጓተት፤ የወጪ መጨመር፤ የጊዜ መራዘም እና ሌሎች ሃብቶችንም በአግባቡ አለመጠቀምን አስከትሏል፡፡

## የፕሮጀክቶች የአዋጪነት ጥናትን በተመለከተ

48. የአገዳ ተክል ልማትና የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ከፕሮጀክት ትግበራው በፊት መከናወንና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

49. ኮርፖሬሽኑ ባጠናው እና እየተገበረ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት  የተቀናጀ ውጤታማና ተቀባይነት ያለው  የፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም በተጨባጭ እየተከናወነ ያለው ግን የአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ሳይጠና ወደ ስራ የተገባ መሆኑን ነው፡፡

50.በኦዲቱ ወቅት በጣና በለስ እና ኦሞ ኩራዝ ስኳር ፕሮጀክት የአገዳ ተክል ልማትና የመስኖ ልማት ወደ ትግባራ ከመገባቱ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ያልተከናወነ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

51. ይህንን በተመለከተ የፕሮጀክቶች ዕቅድና ክትትል ዳይሬክቶሬት በቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ እነዚህ አዳዳስ ፕሮጀክቶች በፈጣን አካሄድ ለመተግበር ሲባል የአዋጭነት ጥናት፤

ዲዛይን እና ግንባታ ጉን ለጉን እየተሰራ ስለሆነ ወደ ትግባራ ከመገባቱ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ያልተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

52. የአገዳ ተክል ልማት የአዋጭነት ጥናቱ (Feasibility study) አስቀድሞ ባለመካሄዱ የአካባቢው የአፈር አይነት እና አየር ሁኔታ ባላገናዘበ መልኩ አገዳ ተክላ መከናወን፣ የአገዳ ተክል ልማት ምርት ግብዓት መጠን አጠቃቀም ወጥ አለመሆን እና በአገዳ ተክል ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

53. የመስኖ ግንባታ የአዋጭነት ጥናት በቅድሚያ ያለመከናወኑ ፕሮጀክቱ የሚስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም፤ በአካባቢ ላይ የሚስከትለውን ተጽዕኖ በቅድሚያ ለመገንዘብ ስለማያስችል የቅድመ ጥንቃቄና መከላከያ ተግባራትን ለማከናወን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቶቹ ለማስፈጸም የጊዜ መጓተትና አላስፈላጊ ወጪ ያስከትላል፡፡

## የፕሮጀክቶች የዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ

54. ወደ ትግባራ ከመገባቱ በፊት የአገዳ ተክል ልማት፤ መስኖ ግንባታና የፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል የፕሮጀክቶች ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ ሊከናወን ይገባል፡፡

55. ኮርፖሬሽኑ ባጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት ኮርፖሬሽኑ የአገዳ ተክልና መስኖ ልማት ዝርዝር ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅትና የቴክኖሎጂ መረጣ በማከናወን በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ 25,000 ሄክታር ለመስኖ ልማት ዝግጁ ማድረግ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ሆኖም በተጨባጭ ለአዳዲስ ስኳር ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባቱ አስቀድሞ ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ እንደማይከናወን ከሥራ ተቋራጮች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

56. የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ወደ ትግባራ ከመገባቱ በፊት የዲዛይን ጥናት ባለመከናወኑ የአገዳ ተክል ልማት ፕሮጀክት አጠቃለይ ማሳ ውስጥ ሥራው በሚያከናውኑበት ወቅት የውሃ ማፋሰሻ (drainage structure) እና የውስጥ ለውስጥ መንገድ ስራዎች በዲዛይን መካተት ሲገባቸው ያልተካተቱ መሆናቸው በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

57. የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ወደ ትግባራ ከመግባቱ አስቀድሞ የዝርዝር ዲዘይን ጥናት (Detail Design Engineering) በመስኖ ግንባታ ላይ ያልተከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት የዲዛይን ጥናቱ ከትግበራው ጋር ጉን ለጉን የሚከናወን በመሆኑ ስራው በየጊዜው የሚቀያየር መሆኑ፤ ለዚህም እንደማሳያነት ለመጥቀስ ከSurface irrigation ወደ ርጭት መስኖ ዘዴ (Sprinkler)፤ ደለል ማስወገጃ (Sediment settling Basin) በኮንክሪት ይገነባል የተባለው

ወደ ጂኦሜንቤሬን (Geomebrane)[1] በመቀየሩ ምክንያት በክረምት ወቅት በጐርፍ የተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡



ፎቶ 2. በኮንክሪት ይገነባል የተባለው የደለል ማስወገጃ (Sediment settling Basin) ወደ ጂኦሜንቤሬን (Geomebrane) መቀየር ምክንያት በክረምት ወቅት በጐርፍ ተወስዶ በድጋሚ በኮንክሪት የተገነባው የደለል ማስወገጃ (Sediment settling Basin) በከፊል.

58. የጣና በለስ እና ኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ ጥናት ባለማከናወኑና ስራውንም ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ባለመዘረጋቱ የሚከተሉት ችግሮች ተስተውለዋል፡-

- ዋናው የመስኖ ውሃ ከጣና ወንዝ ከተቀለበሰበት (Head work) ጀምሮ እስከ ደለል ማስወገጃ (Sediment settling Basin) እንዲሁም ከዚያ በኋላ የሚገኘውም ካናል በደለል የተሞላ መሆኑን፤
- ዋና የውሃ መውሰጃ ካናሎችን ከደለል ለመከላከል የሚያስችል የድሬኔጅ ስራ ባለመሰራቱ ካናሎቹ በደለል የተሞሉበት ሁኔታ መኖሩ፤
- የዋናው ካናል (Head work) ላይ የተሰራው Gate Installation በኤሌክትሮ መካኒካል ችግር የካናሉ በሮቹ በትክክል የማይሰሩ መሆኑ፤
- ዋናው የመስኖ ካናል (Headwork) ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ 30 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው ሲሆን ወደ ካናሉ የሚያስገባ ወጥ የሆነ መንገድ (Access Road) አለመኖር፤

[1] Geomebrane ማለት ለመስኖ መስሪያነት የሚያገለግል ጠንካራ ላስቲክ ነው፡፡

- ባለ አምስት በር intake canal የውሃ ማስተንፈሻ (Escape canal) ባለመኖሩ intake canal በደለል የተሞላ መሆኑ ታውቋል፡፡



ፎቶ 3. ጣና በለስ የስኳር ልማት ፕሮጀክት በደለል ከተሞላው ዋናው ካናል በከፊል

59. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፕሮጀክት የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይን የተዘጋጀለት ቢሆንም በጥናቱ ላይ ከአዋሽ የተጠለፈው የመስኖ ዋና ቦይ ወደ 14.5 ኪ.ሜ የሚሆን በመጀመሪያው ጥናት በኮንክሪት እንደሚገነባ የተገለጸ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት በGeomembrane ወደ 10 ኪ.ሜ. በላይ የሚሆን ያለ ጥናት መገንባቱን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
60. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ማስፋፊያ ፕሮጀክት የመስኖ ግንባታ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ላይ የወለንጪቲ አካባቢ Primary canal 1 እና Primary canal 2 6240 ሄክታር በጥናቱ ቢካተትም በተለያዩ ምክንያቶች ስራው በመንተቱ በአዲስ መልክ በተመረጡ አካባቢዎች ኡላጋ፤ ጠደቻ፤ ወሌንሶ እና Primary canal 3 (ቦፋ) አካባቢ 6600 ሄክታር መሬት ላይ የአዋጭነት ጥናትና የዝርዝር ዲዛይን (detail engineering design) ጥናት ባልተጠናበት ሁኔታ የማልማት ስራው እየተከናወነ መሆኑ በመስክ ጉብኝት ወቅት ከአማካሪ መሃንዲስ ጋር በተደረገ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡
61. ይህንን በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ፤ ጣና በለስ እና የወንጂ/ሸዋ የመስኖ ግንባታ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የዝርዝር ዲዛይን ጥናት (Detail Design Engineering) ከፕሮጀክቶቹ ጎን ለጎን የሚከናወን በመሆኑ ትግበራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

62.የስኳር ልማት ፕሮጀክት የአገዳ ተክልና የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት ወደ ትግባራ ከመግባቱ አስቀድሞ የዝርዝር ዲዛይን ጥናት (Detail Design Engineering) እና የቴክኖሎጂ መረጣ ጥናት ባለመከናወኑ ዲዛይን በተደጋጋሚ መቀያየር፤ ትክክለኛውን የግንባታ ግብዓት መጠቀም አለመቻል፤ በየጊዜው ደለል ዋናው የመስኖ ካናሉ ውስጥ በመግባት ካናሉን ለማጽዳት ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን፤ የፕሮጀክቶች የሥራ ለውጥ ሲደረግ በጥናት የተደገፈ ባለመሆኑ የግንባታ ጥራት ላይ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ ፕሮጀክቶቹን ለተጨማሪ ወጪና ጊዜ የሚዳርግ ይሆናል፡፡

## የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ መኖሩን በተመለከተ

63.የፋብሪካ ግንባታ የስራ ሂደትን ለማጠናከር እና ውጤታማ የማሽነሪ ፋብሪኬሽን፤ የአቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታ፤ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የፕሮጀክት ሥራ የአመራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

64.ኮርፖሬሽኑ ባጠናውና እየተገበረ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውስጥ ከሚመለከተው የስራ ሂደት ባለቤት ጋር የተቀናጀ ፕሮጀክትን ለመምራትና የማስፈጸም አቅምና ብቃትን ለማጎልበት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በመዘርጋት ተግባራዊ እንደሚዳረግ ተገልጿል፡፡

65.በኦዲቱ ወቅት በጣና በለስና በኩራዝ የፋብሪካ ግንባታ በኮርፖሬሽኑ በኩል ምንም አይነት የፋብሪካ ስታንደርድ ባለመኖሩ መካተት ያለባቸው ሥራዎች እንዲከተቱ ያልተደረገ እና በዲዛይን ሥራ ወቅት የሥራ ተቋራጩ በራሱ ያገኛቸውን ስታንደርዶች በመጠቀም እየሰራ መሆኑ እና በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጅክትና በጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት የፋብሪካ ግንባታ የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) አለመኖሩ ተውቋል፡፡

66.በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ለጣና በለስ ፕሮጀክቶች የሚቀርበው ዕቃ ዘግይቶ በመቅረቡ በማሳ ቱቦ ቀበራ ስራ፤ በፓምፕ ተከላ ሥራና በስፐሊክለር ዝርጋታ ስራዎች ላይ መጓተት መፈጠሩ፣ የቱቦ አቅርቦቱ በአብዛኛው በሁሉም ሰከንዳሪ ካናል የተሟላ ሲሆን ነገር ግን (Fittings) ፓምፖችንና የፕላስቲክ ቧንቧ (PVC) ቱቦዎችን ለማገናኘት የሚያስችል እቃዎች እጥረት መኖሩ በኦዲቱ ወቅት በመጠይቅና በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

67.በስኳር ልማት ፕሮጀክት አካል የሆኑት የመስኖ ልማት፣ የአገዳ ተክል እና የፋብሪካ ግንባታ ስራዎችን በትክክል እና ሥራዎችን በቅንጅት ባለመታቀዳቸውና አፈጻጸሙ ቅደም ተከተል ጠብቆ ባለመተግበሩ የአንዱ አፈጻጸም መዘግየት በሌላው ሥራ አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ ከተከለሰ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68.በዚህም ምክንያት ጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት በ2003 በበጀት ዓመቱ በነበረው የመስኖ ልማት መጓተት የተነሳ ቀድሞ 2 ሺህ ሄክታር ልማትና ተከላ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በመስኖ ሥራ መጓተት ምክንያት የተከላው ሥራ በእቅዱ መሠረት መከናወን እንደማይቻል ታምኖበት ዕቅዱ ወደ 230 ሄክታር መውረዱ እና መትከል የተቻለው 86 ሄክታር ብቻ መሆኑን ከአፈጻጸም ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

69.እንዲሁም በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የማስፋፊያ ፕሮጀክት የወለንጪቲ ቦፋ የመስኖ እርሻ ማስፋፊያ ፕሮጀክት በሥራ ተቋራጩ (በኮንትራክተሩ) በ2005 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ የተያዘ ቢሆንም የፕሮጀክቱን የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ለአገዳ ተከላ ኮንትራክተሩ አጠናቆ ስላላስረከበ የእርሻና የአገዳ ተከላ ዕቅድን ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን ከቀረበ የአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

70.በተጨማሪም በተንዳሆ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት በታቀደለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት 5164.09 ሄክታር መሬት የለማ የሸንኮራ አገዳ ምርት ዕድሜው በመራዘሙ እንዲወገድ በመደረጉ 102,440,145.00 ብር ፋብሪካው ማግኘት የሚባውን ገቢ ተገቢ ባልሆነ መልኩ ያሳጣው መሆኑን የፕሮጀክት ጽ/ቤት ካዘጋጀው የዳሰሳ ጥናት ለማወቅ ተችሏል፡፡

71.በኮርፖሬሽኑ በኩል የመስኖ ግንባታ፣የአገዳ ተክል ልማት እና የፋብሪካ ግንባታ የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ባለመኖሩ ለየፕሮጀክቶቹ ግብዓት አቅርቦት ተለይተው የማይታወቁ፤ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፤ ቅደም ተከተል የጠበቀ የማቴሪያል አቅርቦት አለመኖር፣ የሥራ ተቋራጮች አፈጻጸም ቅደም ተከተል እንዲዛባ ማድረጉ እና ዋናው ኮንትራክተሩ እና ንዑስ ተቋራጮች ስራውን በዕቅድ ተቀናጅተው ያለመፈጸማቸው ለፕሮጀክት አፈጻጸም መዘግየት እና ለሐብት አላግባብ መባከን ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

## የፕሮጀክቶቹ ስራ በውሉ በተጠቀሰው ዋጋ እና ጊዜ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ

72. የተቀናጀ የክትትልና ቁጥጥር የአሰራር ሥርዓት በመፍጠር የአዳዲስ ፋብሪካዎች ዲዛይን፤ ማሽነሪ ፋብሪኬሽንና አቅርቦት፤ የግንባታ እና ኮሚሽኒግ ሥራ በውሉ መሰረት በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ በተቀመጠው ዋጋ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

73. ኮርፖሬሽኑ ባጠናውና እየተገበረ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት የተቀናጀ የክትትልና ቁጥጥር የአሰራርና አደረጃጀት ሥርዓት በመፍጠር የአዳዲስ ፋብሪካን

ዲዛይን፣ ማሽነሪ ፋብሪኬሽንና አቅርቦት፣ የግንባታ እና ኮሚሽኒግ ሥራ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ቢታቀድም በተግባር ግን ፕሮጀክቶቹ በውሉ ከተቀመጠ ጊዜ በላይ ወስደዋል፡፡

74. በስኳር ኮርፖሬሽን እና በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን መካከል በተደረገ የውል ስምምነት አስር የስኳር ፋብሪካዎችን ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ በተሟላ መንገድ (Turnkey)[2] ገንብቶና ኮሚሽን አድርጎ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ተዋውለዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከሰም፣ በለስ ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 መጋቢት 2003 ዓ.ም ሥራው ተጀምሮ እስከ ነሃሴ 2005 ዓ.ም ለማጠናቀቅ፣ወልቃይት-ቁጥር1፣ ኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 መስከረም 2004 ዓ.ም ሥራው ተጀምሮ እስከ መጋቢት 2005 ዓ.ም ለማጠናቀቅ፣ ኦሞ ኩራዝ ቁጥር 3፣ ቁጥር 4፣ ቁጥር 5 እና ቁጥር 6 ጥር 2004 ዓ.ም ሥራው ተጀምሮ እስከ ሐምሌ 2005 ዓ.ም ለማጠናቀቅ የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም ስራው ግን በውል በተጠቀሰው ጊዜ አለመጀመሩ እና በተባለው ጊዜ አለመጠናቀቁ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

75. በወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና በ UTTAM Suerotech international Pvt ltd መካከል የስኳር ፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን በተደረገ የውል ስምምነት ከ12/05/2000 ዓ.ም እስከ 13/05/2003 ዓ.ም በተሟላ መንገድ (Turnkey) ገንብቶ እና ኮሚሽን አድርጎ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ የተዋዋሉ ቢሆንም ግንባታው በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቁ፣ ከሚያዝያ 14 2005 ጀምሮ የሙከራ ምርት እንደ ጀመረና ሙሉ በሙሉ ርክክብ ያልተፈጸመ መሆኑ በመስክ ኦዲት ጉብኝት ወቅት ታውቋል፡፡

76. ይህንን በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ፣ ጣና በለስ እና የወንጂ/ሸዋ የፋብሪካ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተቋራጮች አቅም ውስንነት፣ ኮንሰልታንቱ ለስራው ያለው ሱፐርቨዥን ዝቅተኛ መሆን፣ በንዑስ ተቋራጭ የተቀናጀ እና የተጠናከረ የማቴሪያል አቅርቦት እና የተከላ ስራ አለመኖር፣ ቅደም ተከተል የጠበቀ የማቴሪያል አቅርቦት አለመኖር፣ ዋናው ኮንትራክተሩ እና ንዑስ ተቋራጮች ስራውን በዕቅድ ባለመመራታቸውና ክትትል እና ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ለፕሮጀክቶቹ መጓተት ትልቁን ሚና መጫወቱን ገልጸዋል፡፡

77. ከዚህ ጋር በተያያዘ ግንባታውን የሚያከናውነው ተቋራጭ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የግንባታ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጣና በለስ ቁጥር 1፣ ቁጥር 2 እና ኩራዝ ቁጥር 1 የስኳር የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት በውሉ መሰረት ላለመጠናቅ ምክንያቶች በስኳር ኮረፖሬሽን በኩል መሠረታዊ ዲዛይን ለማጽደቅ ረጅም ጊዜ መውሰድ፣ ለፕሮጀክቶቹ

---

[2] Turnkey፡- ውል ተቀባይ የሚገነባቸውን የስኳር ፋብሪካዎች ስራ ሁሉ (ከዲዛይን እስከ ኮሚሽኒንግና ሰው ኃይል ስልጠና ድረስ) አጠናቆ ለውል ሰጪ በቀጥታ ስራ የሚጀምር ፋብሪካ የሚስረከብ የተሟላ ስራ ማለት ነው፡፡

የሚስፈልጉ ክፍያዎች በወቅቱ አለመገኘት፤ የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ እጥረት፤መጠናቀቅ የሚገባቸው ዲዛይኖች በወቅቱ አለመጠናቀቅ፤ የፕሮጀክቶች ፈጻሚ አካላት የአቅም ውስነት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለወንጂ/ሸዋ የፋብሪካ የስራ ተቋራጭ ጋር ቃለ መጠይቅ ለማከናወን ተሞክሮ ተቋራጭ ድርጅቱ ለኦዲት ቡድኑ የስራ ትብብር ባለማድረጉ መረጃ ለመግኘት አልተቻለም፡፡

78.ይህም በአብዛኛው የፋብሪካ ግንባታ ስራ ከተቀመጠላቸው የጊዜ ዕቅድ በላይ መወሰዱ፤ የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከሁለት ዓመት በላይ፤ የጣና በለስ ቁጥር 1፤ ቁጥር 2 እና ኩራዝ ቁጥር 1 ከአስር ወራት በላይ በመጓተታቸው ኮርፖሬሽኑ ለአላስፈላጊ ወጪ ከመዳረጉም በላይ በአምስት ዓመቱ የትራንስፎሜሽን ዕቅድ ላይ የተቀመጠለትን ዕቅድ እንዳያሳካ ያደርገዋል፡፡

79.የፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአፈጻጸም ማንዋል ለግንባታ ሥራ አገልግሎት ግዥ የተፈረመው የውል ስምምነት የዋጋ ማስተካካያ እንደሚደረግ የሚፈቀድ ከሆነ፤ የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለው የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ከ18 ወራት በላይ ሲሆን እና ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ12 ወራት በኂላ ማስተካከል እንደሚቻል ቢገልጽም ኮርፖሬሽኑ በተጨባጭ የዋጋ ማስተካከያ ያደረገባቸው የውል ስምምነቶች ግን ግንባታቸው 18 ወራት በታች መሆናቸው ከተከለሱ ዶክመንቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

80.በስኳር ኮርፖሬሽና በባቱ የኮንስትራክሽን አ.ማ መካከል በተደረገ የውል ስምምነት መሰረት በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የመሬት ድልዳሎ (Land Leveling) የመሬት መሰንጠቅ አገልግሎት በ09/02/2005 ዓ.ም በተፈረመው የውል ስምምነት ከህዳር 1 እስከ ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም አጠናቆ ለማስረከብ በ 25,818,740.00 ብር የተስማማ ሲሆን በ3/07/2005 ዓ.ም ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የዋጋ መስተካከያ ብር 4,181,260.00 የ(16%) ለ1000 ሄክተር የግዥ ስርዓት ባልተከተለ መልኩ ማሻሻያ መደረጉ ታውቋል፡፡

81.በስኳር ኮርፖሬሽና የኮንስትራክሽን ሥራዎችና የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መካከል የተደረገ የወል ስምምነት መሰረት በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የመሬት ድልዳሎ (Land Leveling) አገልግሎት በ09/02/2005 ዓ.ም በተፈረመው የውል ስምምነት ከህዳር 1 - ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ስራውን አጠናቆ ለማስረከብ በ 25,818,740.00 ብር የተስማማ ሲሆን በ3/07/2005 ዓ.ም ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የዋጋ መስተካከያ ብር 4,181,260.00 የ(16%) ለ1000 ሄክታር የግዥ ስርዓት ባልተከተለ መልኩ ማሻሻያ መደረጉን ከተከለሱ የውል ስምምነቶች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

82.ስኳር ኮርፖሬሽንና ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን 10,000 ሄክታር ለማልማት በ2003 ዓ.ም ውል የተፈራረሙና ስራውንም ለማስጀመር 30% ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ሲሆን ተቋራጭ ድርጅቱ በተጨባጭ ያለማው 2000 ሄክታር ሲሆን የተቀረውን 8000 ሄክታር ስኳር ኮርፖሬሽን ለሌሎች ተቋራጮች የሰጠ መሆኑ እና በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ ካለማው የሄክታር መጠን ጋር ተመጣጣኝ አለመሆኑ ከተከለሱ ዶክመንቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

83.ይህንን በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ የግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ የስራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ስለ ጨረታው አሰጣጥ በተመለከተ በግዥ ክፍሉ በኩል የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

84.የግንባታ ስራዎች ከተጀመሩ በኋላ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በሚያጋጥምበት ወቅት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ሲኖሩ በኮርፖሬሽኑ በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% መብለጥ የሌለበት መሆኑ በመንግስት እና በኮርፖሬሽኑ የግዥ መመሪያ ላይ ተጠቅሷል፡፡

85.ለወንጂ ሸዋ ስኳር የመስኖ ማስፋፊያ ፕሮጀክት በመጀመሪያ በ13/10/2002 ዓ.ም የተፈረመው የኮንትራት ውል 6300 ሄክታር መሬት ለማልማት የተመለከተው ዋጋ 799,394,202.51 ብር ሲሆን በተለያየ ጊዜ በተደረገ የዋጋ ማስተካከያ ከመጀመሪያው የውል ዋጋ ጭማሬ ብር 957,767,481.12 (119.81%) የግዥ ስርዓትን ባልተከተለ መልኩ የተደረገ የዋጋ ማስተካከያ መሆኑን ከውል ስምምነቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

86.ይህንን በተመለከተ ወንጂ/ሸዋና የኮርፖሬሽኑ የግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ግዥው በነሱ በኩል ያላለፈና መረጃውም እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

## የፕሮጀክት ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ

87.የአገዳ ተክል ልማት፤ የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የተሰሩ ስራዎች በተቀመጠለት ዲዛይን እና እስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

88.በኦዲቱ ወቅት ኮርፖሬሽኑ ሊያስገነባቸው ላቀደላቸው አስር አዳዲስ የስኳር ፋብሪካ ግንባታዎች ሥራቸው በተጀመረበት ወቅት ጥራት የሚቆጣጠር አማካሪ ድርጅት አለመቀጠሩን ለጣና በለስ ቁጥር 1፤ ቁጥር 2 እና ለኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 የፋብሪካ ግንባታ ስራቸው የተጀመረው መጋቢት 2003 ዓ.ም ሲሆን ኮርፖሬሽኑ አማካሪ ድርጅት የቀጠረው ሥራው ከተጀመረ ከሁለት ዓመት በኋላ ሐምሌ 10 ቀን 2005 ዓ.ም መሆን የኮርፖሬሽኑ የግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

89. የጣና በለስና ኩራዝ ፋብሪካ ግንባታ (ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2006 ጥቅምት ወር ድረስ) በየደረጃው እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች (civil work) በተቀመጠለት ዲዛይንና እስፐሲፊኬሽን መሰረት መሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲስ ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤ እንዲሁም የአዳዲስ ፋብሪካዎች ግንባታ ከመጀመሪያው ጀምሮ ስራው በተቀመጠው የውል ስምምነት መሰረት ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ የቴክኒክ ባለሞያ በፕሮጀክት ቦታው ላይ ያልተመደበ መሆኑ ከመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችላል፡፡

90.ስለሁኔታው የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የግንባታ የዘርፍ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለፋብሪካ ግንባታ ባለሙያ ያልተመደበ ቢሆንም በተቋራጭ ድርጅቱ በኩል ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ ተቆጣጣሪ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

91.እንዲሁም የጣና በለስና ኩራዝ የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት ሥራዎች ከመጀመሪያ ጀምሮ (civil work) በተቀመጠለት ዲዛይንና እስፐሲፊኬሽን መሰረት እንዲከናወን የግንባታ ግብዓቶች (construction material input) የጥራት ማረጋገጫና የግብዓቶች መጠን መለኪያ ላብራቶሪ አለመኖሩ በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

92.የግንባታ ግብዓቶች (construction material input) የጥራት ማረጋገጫና የግብዓቶች መጠን መለኪያ ላብራቶሪ ባለመኖሩ ምክንያት በተቀመጠለት ዲዛይንና እስፐሲፊኬሽን መሰረት ቁጥጥር ለማድረግ ስለማያስችል የግንባታ ፕሮጀክቱ ላይ የጥራት ጉድለት ሊያስከትል ይችላል፡፡

93. የበለስ ስኳር ፕሮጀክት የመስኖ ግንባታን በተመለከተ የ10,000 ሄክታር የሚያለማው የመስኖ ርጭት አጣቃላይ የአቅርቦት እና የግንባታ ሥራውን የሚገልጽ የውል ስምምነት ሰነድ አማካሪ መሃንዲስ ለሆነው ለአማራ የዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ያልተሰጠ መሆኑ፣ አማካሪ መሃንዲሱ በውሉ ስምምነት ሰነድ መሠረት ሥራው ለመፈፀሙ የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ የአማራ የዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስና በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡፤

94.የወንጂ/ሸዋ፣ ጣና በለስና ኩራዝ የፋብሪካ፤ የአገዳ ተክል ልማት ሥራ በፕሮጀክቱ የጥራት ማረጋገጫ ማኑዋል (Quality Assurance Manual) አለመኖሩ ታውቋል፡፡

95. ኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ባለመቅጠሩ ምክንያት የፋብሪካ ግንባታ ከመከናወኑ በፊት ዝርዝር የፋብሪካ ዲዛይን ስራ በአማካሪ ድርጅት ያልተከናወነ ሲሆን ይህ በመሆኑም በጣና በለስና በኩራዝ የፋብሪካ የግንባታ ክንውን በምን ዓይነት የጥራት ደረጃ እንደሚገነባ የማይታወቅ መሆኑን፤የፕሮጀክቶች አፈጻጸም በሚገባው ደረጃ በቦታው ተግኝቶ አፈጻጸማቸውን ከመገምገም ይልቅ በኮንትራክተሮች ሪፖርት ላይ ብቻ የተመረኮዘ ሪፖርትና ትንታኔ የሚደረግ ሲሆን የግንባታ ሥራው በተቀመጠለት ዲዛይን፤ ስፐስፊኬሽን እና በኮንትራት ዶክመንት መሰረት

እየተከናወነ መሆኑ ለማረጋገጥ የሚደረገውን የግንባታ ጥራት ቁጥጥር እና ክትትል ስራ ውስብስብ ያደርገዋል፡፡

96.ኮርፖሬሽኑ ለነባርና አዲስ ለሚተከል የአገዳ ተክል (plant cane) የማዳበሪያ የአጠቃቀም ስታንዳርድ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

97. በጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት የአገዳ ተክል (Plant cane) የማዳበሪያ አጠቃቀም በጥናት የተረጋገጠ ስታንዳርድ የሌለው መሆን፤ በተመሳሳይ የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የአገዳ ተክል (plant cane) የማዳበርያ አሰጣጥ ወቅታዊ አለመደረጉን የፕሮጀክቶቹ የአገዳ ተክል ልማት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

98.የአገዳ ተክል (Plant cane) የማዳበሪያ አጠቃቀም እና የጥራት ማረጋገጫ ማኑዋል ወጥነትና በጥናት የተመሰረተ ያለመሆኑ በማዳበሪያ አጠቃቀምና በጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

## የፕሮጀክቶች ስራ በመንግስት የግዢ መመሪያ መሰረት በጨረታ መሰጠቱን በተመለከተ

99.የአገዳ ተክል ልማት፤ መስኖና ፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት ሥራ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ ለአሸናፊ ድርጅቶች ሊሰጥ ይገባል፡፡

100. ኮርፖሬሽኑ ሊያስገነባቸው ያቀደው አዳዲስና ነባር የስኳር ልማት የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት የወንጂ/ሸዋ ስኳር ማስፋፊያ ፕሮጀክት ለኦሮሚያ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፤ የጣና በለስ ዋና ካናሉ ለአማራ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና የ10000 ሄክታር የርጭት መስኖ ዘዴ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን፤ የወልቃይት የመስኖ ግንባታ ለትግራይ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና የኦሞ ኩራዝ ለደቡብ ብሄር ቤሄረሰቦችና ህዝቦች የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የመንግስት መመሪያ ባልተከተለ መልኩ ያለጨረታ መሰጠቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

101. ጨረታው አሰጣጡ በተመለከተ የግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በግዥ ክፍሉ በኩል የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

102. ከዚህም በተጨማሪ የአስር አዳዲስ የስኳር ፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶች የፋብሪካ ግንባታ ሙሉ ለሙሉ ለብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የመንግስትን የግዥ ስርዓትን ባልተከተለ መልኩ ያለጨረታ መሰጠቱና ስለ ጨረታው አሰጣጥ በግዥ ክፍሉ በኩል የሚታወቅ ነገር እንደሌለ የግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው መጠይቅና ከሰጡት መልስ እና ከተከለሱ ዶክመንቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

103. ኮርፖሬሽኑ የመንግስትን የግዥ መመሪያ ባልተከተለ መልኩ ያለ ጨረታ ለተቋራጮች በመሰጠቱ ፕሮጀክቶቱ በተቀደላቸው ጊዜ እና ወጪ እንዳይጠናቀቁ አስተዋጾኦ ይኖረዋል፡፡

## የፕሮጀክቶች የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ

104. በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለውና ወቅታዊ በሆነ መልኩ የነባሩም ሆነ የአዳዲስ ፕሮጀክቶች መረጃ በማዕከል ደረጃ የመረጃ ቋት /Data base/ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች የሚደርስበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

105. ኮርፖሬሽኑ ባጠናውና እየተገበረ ባለው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት የሥራ ክፍሎች መረጃዎቻቸውን በመረጃ ቋት /Data base/ ማስገባት/ማከማቸት የሚያስችል ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ አስተማማኝ የአመራርና የሰው ኃይል ብቃትን በማጎልበት፤ ውጤታማ አሰራርና አደረጃጀት በመዘርጋት መረጃን መያዝ እንዳለባቸው ተገልፀዋል፡፡

106. ሆኖም በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለውና ወቅታዊ በሆነ መልኩ የነባሩና የአዳዲስ ፕሮጀክቶች የመረጃ ቋት /Database/ በማዕከል ደረጃ ያልተዘጋጀና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ዶክመንቶችና መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

107. ኮርፖሬሽኑ የነባሩና የአዳዲስ ፕሮጀክቶች ወቅታዊ የስራ ደረጃዎችን የሚያሳይ መረጃ አጠናቅሮ በማዕከል ደረጃ ያለመያዙ የፕሮጀክቶችን  የስራ ደረጃ ለመከታተል እና ለመገምገም አያስችልም፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

በናሙና ተመርጠው በታዩ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸምን በተመለከተ የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች (አገዳ ተክል ልማት፣ ፋብሪካ ግንባታ እና የመስኖ ልማት) የፕሮጀክቶችን ዝርዝር ጥናት በማከናወን የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል እና ሃብት ያገናዘበና አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳይ መሪ ዕቅድ (Master plan) ያልተዘጋጀ መሆኑ፡፡
- የአገዳ ተክል ልማት፤ የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት ተግባሪዊ አለመደረግ፡፡ የበለስ ስኳር ልማት ፕሮጅክት እና የኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጅክት የአገዳ ተክል ልማት ፕሮጀክት ዕቅድ በኮርፖሬሽን ደረጃ ታቅዶ ለፕሮጀክቶቹ የሚላክ መሆኑና የሚያስፈጽሙ አካላትን በዝግጅት ወቅት የማያሳትፍና ያለውን የማስፈጸም አቅም ግንዘቤ ውስጥ ባለማስገባቱ እና ከሌሎች (መስኖና ከፋብሪካ ግንባታ) ጋር ቅንጀታዊ አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የሚያስገነባቸውን የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ በተመለከተ የአፈጻጸም ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብና በሪፖርቱ መሰረት ግምገማ የማይደረግ መሆኑ፤
- የአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ሪፖርት ይዘት የፋይናንስና የፊዚካል አፈጻጸሙን በሚያሳይ መልኩ የማይዘጋጅ መሆኑ፡፡
- በኮርፖሬሽኑ ደረጃም ሆነ በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጅክትና በጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት የአገዳ ተክል፣ የመስኖ ግንባታ፣ የፋብሪካ ግንባታ የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ያልተዘጋጀ መሆኑ፣ ፕሮጀክቶችን በሚገባ ባለማቀድ፣ የተቀናጀ ትግበራ ባለማከናወን የተለያዩ ስራዎች ቅደም ተከተል ጠብቀው አለመተግበራቸው፣
- በአዳዲስ ስኳር ልማት ፕሮጅክቶች የአገዳ ተክል ልማትና የመስኖ ግንባታ በተመለከተ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ያልተጠና መሆኑ፣
- በአዳዲስ ስኳር ልማት ፕሮጅክቶች ወጥነት ያለው የማዳበሪያ አጠቃቀም አለመኖር፤ የአካበቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተጠና ስታንዳርድ ያለው የማዳበሪያ አጠቃቀም ስርዓት አለመኖር፤
- በነባር ፕሮጀክቶች በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ፕሮጀክት የአገዳ ተክል (Plant cane) የማዳበሪያ አጠቃቀም ወቅታዊ ያልተደረገ በመሆኑ ምክንያት፤ ለአገዳ ተክል የሚደረገው

እንክበካቤ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑና በተመሳሳይ የመስኖ ግንባታው አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ያልተጠና በመሆኑ ሊካተቱ የሚገባቸው ሥራዎች ሳይከተቱ መቅረታቸው፤ ላልታሰበ ወጪ መጨመር እና ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ ሰሌዳ ውስጥ እንዳይጠናቀቁና የጊዜ መራዘም ማስከተሉ፤

- አዳዲስ የፋብሪካ ግንባታ ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል መሠረታዊ ፤ የዝርዝር ዲዛይን ዝግጅት እና ቴክኖሎጂ መረጣ ባለመደረጉ የስራ ታቋራጩ በምን መልኩ ክንውኑን እንደሚያከሄድ ግልጽ አለመሆኑ፤
- የጣና በለስ እና ኦሞ ኩራዝ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል የአዋጭነት ጥናት፤ ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ ጥናት ከትግበራ በፊት አስቀድሞ ባለመዘጋጀቱ የዲዛይን ስራው ጋር ጐን ለጐን የሚከናወን መሆኑ፣ ይህም በመሆኑ በአፈጻጸም ላይ የጊዜ መርዘም እና ለወጪ መጨመር ምክንያት መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውናቸው የአዳዲስ የስኳር ፋብሪካ  ግንባታ ፕሮጀክቶች የማሽነሪ ፋብሪኬሽን ስራዎች በባለቤትነት ብረታ ብረትና ኢንጂኔሪንግ ኮርፖሬሽን የተሰጠ ቢሆንም ይህንንም ሥራ በተቀመጠው የውል ስምምነት፤ የዲዛይንና እስፔስፊኬሽን መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ አማካሪ መሀንዲስ እና የኮርፖሬሽኑ ባለሞያ አለመኖሩ የግንባታ ሥራ ሂደት እና ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር መሆኑ፤
- የአገዳ ተክልና መስኖ ልማት ግንባታ ወደ ትግባራ ከመግባቱ አስቀድሞ ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት፤ የቴክኖሎጂ መረጣ ባለመደረጉ በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት በትግበራ ወቅት የውሃ ማፋሰሻ (drainage structure) ባለመካተቱ የአገዳ ተክል የእርሻ ማሳ ውስጥ አላስፈላጊ ውሃና ደለል በማሳ ውስጥ የተኛ በመሆኑ በአገዳ ተክል ልማት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ።
- በስኳር ኮርፖሬሽን የሚገነቡ የጣና በለስ እና የኩራዝ የስኳር ፋብሪካ የግንባታ ስራዎች ሙሉ በሙሉ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የመንግስትን የግዥ ስርዓትን ሳይከተል  ያለ ምንም ጨረታ በቀጥታ የተሰጠ መሆኑ፤
- ለፋብሪካ ግንባታ ሥራ የዲዛይን፤ ማሽነሪ ፋብሪኬሽንና አቅርቦት፤ የግንባታ እና ኮሚሽኒግ ሥራ በኮርፖሬሽኑ በኩል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት እና ከሥራ ተቋራጩ ጋር የተቀናጀ አሰራር ያለመኖሩ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ በ18 ወራት እና በተያዘለት ወጪ እንዳይጠናቀቅ ማድረጉ።
- ኮርፖሬሽኑ የሚያስገነባቸውን የመስኖና የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጅክቶች ከስራ ተቋራጮች እና ካሉት ተቆጣጠር መሃንዲሶች ጋር የተቀናጀ የክትትልና የቁጥጥር አሰራርና ሥርዓት ባለመኖሩ በውሉ መሰረት የአዳዲስ እና ነባር የፕሮጀክቶች ግንባታ ሥራ ከታቀደለቸው መጠን በላይ ወጪ መጨመር እና በተቀመጠላቸው ጊዜ ሰሌዳ ውስጥ የማይጠናቀቁ መሆኑ፤

- በጣና በለስ እና ኩራዝ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ የመጀመሪያው የውል ስምምነት ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት 12 ወራት ሳይሞላ 8.1% የዋጋ ጭማሪ መደረጉ እንዲሁም በ18 ወራት ለሚያልቅ የግንባታ ፕሮጀክቶች የዋጋ ማስተካከያ መደረጉ ሳልተገባ ወጪ የዳረገ መሆኑ፤
- በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ፕሮጅክት ከመጀመሪያው ውል ዋጋ 799,394,202.51 ብር በመጨመር ብር 957,767,481.12 (119.81%) ጭማሪ ማሳየቱ ይህም የግዥ መመሪያ ከሚፈቅደው 30% በላይ ጭማሪ ያሳየ መሆኑ፤
- ለአዳዲስ የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የሚፈጽማቸው ስራዎች በተቀመጠው ዲዛይን እና እስፔሲፊኬሽን መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ ከመጀመሪያ ጀምሮ ያልተቀጠረ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የሚያስገነባቸውን ፕሮጀክቶች ወጥነትና ወቅታዊ የስራ ደረጃን በሚገልጽ መልኩ የነባሩም ሆነ የአዳዲስ ፕሮጀክቶች የመረጃ ቋት /Database/ በማዕከል ደረጃ በተደራጀ መልኩ የሚያዝበት ስርዓት ያለመዘርጋቱ፤

ስለሆነም ከላይ የተገለጹትን በስኳር ልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ የታዩትን ጉድለቶችን ለማስወገድ ወይም ለማስተካከል ይረዳሉ ብለን ያስብናቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## *የማሻሻያ ሃሳቦች*

- ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች (አገዳ ተክል ልማት፣ ፋብሪካ ግንባታ እና የመስኖ ልማት) አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት በኢኮኖሚ በብቃትና በጥራት ለማከናወን፤መሪ ዕቅድ (Master plan) በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማደረግ አለበት፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ዕቅድ ሲያዘጋጅ የፕሮጅክቶቹን ፈጻሚ አካላት ባሳተፈ መልኩ እና ያለውን የማስፈጸም አቅም በማገናዘብ ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በቅንጅት ሊሆን ይገባል፡፡
- የአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ሪፖርት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸሙን በሚያሳይ መልኩ መዘጋጀትና መቅረብ አለበት፡፡
- የአገዳ ተክል፤ የመስኖና የፋብሪካ ግንባታ የፕሮጀክት የስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) የስራውን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ በዝርዝር መልኩ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በኮርፖሬሽኑ በስሩ ለሚከናወኑ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ትግባራ ከመግባቱ አስቀድሞ የአገዳ ተክልና የመስኖ ልማት የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ማከናውንና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡
- በነባሮችም ይሁን በአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአገዳ ተክል (Plant cane) የማዳበሪያ አጠቃቀም የአካበቢውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሊጠናና ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ትግባራ ከመግባቱ አስቀድሞ የአገዳ ተክልና መስኖ ልማት ግንባታ ለማከናወን የሚያስችል ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት፤ የቴክኖሎጂ መረጣ ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- የፋብሪካ ግንባታ የስራ ሂደትን ለማጠናከር እና ውጤታማ የማሽነሪ ፋብሪኬሽን፤ የአቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታ፤ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለማቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የአዳዲስ ፋብሪካዎች ግንባታ የማሽነሪ ፋብሪኬሽን ሥራ የዲዛይንና እስፐስፊኬሽን ጥናት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ የማሽነሪ ፋብሪኬሽን ስራውም በተቀመጠው የውል ስምምነት በዲዛይንና እስፐስፊኬሽን መሠረት መከናወኑ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ለአዳዲስ ስኳር ፕሮጀክቶች የመስኖና የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶች ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሊቀጠርና በየደረጃው የሚሰሩ ስራዎች በተቀመጠለት ዲዛይን እና እስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑ በተቆጣጠሪው መሃንዲስ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- የአገዳ ተክል ልማት፤ መስኖና ፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት ለሥራ ተቋራጮች በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት በጨረታ ለአሸናፊ ድርጅቶች መስጠት አለበት፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሚያስገነባቸው የፋብሪካ ግንባታ ስራ የዋጋ ማስተካከያ በኮርፖሬሽኑ የግዥ መመሪያ መሠረት ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- የግንባታ ስራዎች ከተጀመሩ በኂላ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በሚያጋጥምበት ወቅት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ሲኖሩ በኮርፖሬሽኑ በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን በመንግሥት ግዥ መመሪያ መሠረት ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% በላይ መብለጥ የለበትም፡፡
- በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለውና ወቅታዊ የስራ ደረጃን በሚገልጽ መልኩ የነባሩም ሆነ የአዳዲስ ፕሮጀክቶች መረጃ ከየሥራ ክፍሉ ወደ የመረጃ ቋት /Data base/ በማስገባት በማዕከል ደረጃ ሊዘጋጅና ለተጠቃሚዎች የሚደርስበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የስኳር ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው ነባርና አዳዲስ የስኳር ፋብሪካ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪዎች

## አባሪ 1. የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

**የኦዲት አካባቢ**:- "የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተመለከተ የዘረጋው የአሠራር ስርዓት በቁጠባ፤ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም"


| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| 1. የአገዳ ተክል ልማት ተግባርን በቁጠባ፤ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፤ | 1.1 የአገዳ ተክል ልማት ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት ተግባሪዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.2 የአገዳ ተክል ልማት የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ሊኖርና ተግባሪዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.3 የአገዳ ተክል ልማት የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ማከናውንና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.4 በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ የስኳር ልማት ፕሮጅክቶች በዕቅዱ መሠረት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ትግበራ ሳይገቡ የቆዩ የፕሮክቶች ዝርዝር ዲዛይን እና የአዋጭናት ጥናት ክለሳ (Review) ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ |
| | 1.5 የአገዳ ተክል ልማት ፕሮጀክት የጨረታ አሰጣጥ ሂደት በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ለአሸናፊ ድርጅቶች ሊሰጥና ውል ሊፈረም ይገባል፡፡ |
| | 1.6 የአገዳ ተክል ልማት ፕሮጀክት የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በሚያደርግበት ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታው ሥራ ጠቅላላ የውል ዋጋ 25% የግዥ መጠን ቀደም ሲል ከተገዛው መብለጥ የለበትም፡፡ |
| | 1.7 ለነባርና አዲስ ለሚተከል የአገዳ ተክል (plant cane) የማዳበሪያ የአጠቃቀም ስታንዳርድ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 2. የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጅክት ተግባርን በቁጠባ፤ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፤ | 2.1 የፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል የአዋጭነት ጥናት ሊጠነና፤ ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.2 የፋብሪካ ግንባታ የስራ ሂደትን ለማጠናከር እና ውጤታማ የማሽነሪ ፋብሪኬሽን፤ የአቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታ፤ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለማቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.3 የፋብሪካ ግንባታ ከመከናወኑ በፊት የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር የዲዛይን ስራ በኮርፖሬሽኑ ባለሙያዎች (በአማካሪ |

| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | ድርጅት) ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 2.4 የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት የጨረታ አሰጣጥ ሆነ የአገልግሎት (ተቋራጭና አማካሪ) ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ለአሸናፊ ድርጅቶች ሊሰጥና ውል ሊፈረም ይገባል፡፡ |
| | 2.5 የግንባታ ስራ የዋጋ ማስተካከያ ተግባሪዊ ሊደረግ የሚችለው የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ከ18 ወራት በላይ ሲሆን እና ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ12 ወራት በኋላ መሆን ይገባል፡፡ |
| | 2.6 የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በሚያደርግበት ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታው ሥራ ጠቅላላ የውል ዋጋ 25% የግዥ መጠን ቀደም ሲል ከተገዛው መብለጥ የለበትም፡፡ |
| | 2.7 የግንባታ ስራዎች ከተጀመሩ በኋላ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በሚያጋጥምበት ወቅት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ሲኖሩ በኮርፖሬሽኑ በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% መብለጥ የለበትም፡፡ |
| | 2.8 የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በማድርግ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ 25% በሚበልጥበት ጊዜ የዋጋ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን በጥናት በመረጋገጥ ተገቢውን ውሳኔ መወሰን እንዲችል ለኮርፖሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር ቀርቦ ሊወሰን ይገባል፡፡ |
| | 2.9 ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው ለማናቸውም ዓይነት የአገልግሎትና የፕሮጀክቶች ግንባታ ክፍያን ሲያከናውን ከክፍያው ላይ ተገቢ የሆነውን የቅድሚያ የገቢ ግብር ተቀናሽ (withhold) እና ተጨማሪ ዕሴት ታክስ (VAT) ለመንግስት ገቢ ማድረግ ይገባል ፡፡ |
| 3. የመስኖ፣ ቤቶችና መሰረተ ልማት ግንባታን በቁጠባ፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፤ | 3.1 የመስኖ ልማት የግንባታ ስራዎች ዕቅድ ሊኖረውና በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረትም ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.2 የመስኖ ልማት ግንባታ ለማከናወን የሚያስችል የአዋጭነት ጥናት ሊጠናና ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣ ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 3.3 የመስኖ ልማት ስራዎች ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅትና የቴክኖሎጂ መረጣ በተዘረጋው የአሰራር ማኑዋል መሰረት ተግባሪዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | 3.4 የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት የጨረታ አሰጣጥ ሂደት በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ለአሸናፊ ድርጅቶች ሊሰጥና ውል ሊፈራረም ይገባል፡፡ |
| | 3.5 የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በሚያደርግበት ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታው ሥራ ጠቅላላ የውል ዋጋ 25% የግዥ መጠን ቀደም ሲል ከተገዛው መብለጥ የለበትም፡፡ |
| | 3.6 ከግድብ ጀምሮ በካናልና በየደረጃው በተዘጋጁ የተለያዩ የመስኖ ቦዬችና ቱቦዎች የመስኖ ውሃ ወደ አገዳ የሚደርሰው በውል ስምምነት መሰረት ሊገነቡ ይገባል፡፡ |
| | 3.7 በመስኖ ሥራ ሂደት ውስጥ ከሚካቱቱት የሥራ ዓይነቶች አንዱና ዋነኛ የሆነው በየዕለቱ የሚፈለገውን የውሃ መጠን ከዋና ቦይ ወደ ተቀዳሚ ቦይ የሚመጣ ውሃን የሚቆጣጠር ተገቢው የሆነ የሰው ኃይል ሊመደብ ይገባል፡፡ |
| 4. የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ክትትል፤ ቁጥጥርና የድጋፍ ሥራ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም ከባለድርሻ አካለት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤ | 4.1 ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች (አገዳ ተክል ልማት፣ ፋብሪካ ግንባታ እና የመስኖ ልማት) አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳይ መሪ ዕቅድ (Master plan) በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀትና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 4.2 የአገዳ ተክል ልማት፤የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የተሰሩ ስራዎች በተቀመጠለት ዲዛይን እና እስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 4.3 የአገዳ ተክል ልማት፤ የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ በየደረጃው ለሚፈጽማቸው ክፍያ ለተ ትክክለኝነት በተቆጣጣሪ መሀንዲሱ ከተረጋገጠ በኋላ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 4.4 ለአገዳ ተክል ልማት እና ለመስኖ ግንባታ ተነሽ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሠፈራና መልሶ ማቋቋሚያ የአሰራር መመሪያ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 4.5 የንብረት ግምትና የካሳ ክፍያ አፈፃፀም ስርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 4.6 ለአገዳ ተክል ልማትና ለመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ ለሚውለው ስፍራ የሚገኙ ነዋሪዎች እና በዚሁ ግንባታ ምክንያት ከቦታቸው ለሚፈናቀሉ የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲከፈል በመንግሥት የተፈቀደው ካሣ /Compensation/ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊከፈልና ቦታው ለተፈለገው ሥራ ነፃ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 4.7 ለሰፈራ የተመዘገቡ ፈቃደኛ አርሶ አደሮችን ዝርዝር መረጃ (በስም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በቤተሰብ፤ በሀብት፣ በዕዳ እና የመሬት ይዞታን) በጥራት ተመዝግቦ በኮርፖሬሽኑ መያዝ |

| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | ይገባዋል። |
| | 4.8 ለአርሶ አደሩ የተመረጡ የሰፈራ ቦታዎችን በመንደር በማደራጀት የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማት ተቋማትን /የውሃ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የእምነት ተቋም፣ መንገድ/ በቅድሚያ ሊዘጋጅ ይገባል። |
| | 4.9 በአገዳ ተክል ልማት ቀጣይነትና ጥራት ያለው ምርት ማግኘት እንዲቻል የማሳ ስንጣቆና ድልዳሎ ስራ በዕቅድ ሊመራና በተቀመጠለት የውል ስምምነት መሠረት ክትትል ለደረግ ይገባል። |
| | 4.10 ለአገዳ ተከላ የተዘጋጀው ማሣ ውሃ የማይተኛበትና በተቀመጠው ስታንዳርድና በውል ስምምነቱ መሰረት የማጠንፈፊያ ቦይ (drain) ሊኖረውና ሊገነባ ይገባል። |
| | 4.11 የተቀናጀ ክትትልና ቁጥጥር አሰራርና ሥርዓትን በመፍጠር በውሉ መሰረት የአዳዲስ ፋብሪካን ዲዛይን፤ ማሽነሪ ፋብሪኬሽንና አቅርቦት፤ የግንባታ እና ኮሚሽኒግ ሥራ በ18 ወር ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቅ ይገባል። |
| | 4.12 የተቀናጀ ክትትልና ቁጥጥር አሰራርና ሥርዓትን በመፍጠር በውሉ መሰረት የአዳዲስ እና ነባር የፕሮጀክቶች ግንባታ ሥራ በታቀደው ገንዘብና ጊዜ ሊጠናቀቅ ይገባል። |
| | 4.13 ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውናቸው ነባርና የአዳዲስ ፋብሪካዎች ግንባታ የማሽነሪ ፋብሪኬሽን ስራው በተቀመጠው የውል ስምምነት መሰረት ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ የቴክኒክ ባለሞያ ሊኖርና በዚህም በሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። |
| | 4.14 ኮርፖሬሽኑ የሚያስገነባቸውን የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ በተመለከተ በየወሩ ለቀርብና ሪፖርቱ መሰረት ግምገማ ሊከናወን ይገባል። |
| | 4.15 በስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ ችግሮችን ኮርፖሬሽኑ በወቅቱ ከአማካሪው መሃንዲሶቹ እና ከስራ ተቋራጭ ጋር በመሆን ወቅታዊ መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል። |
| | 4.16 በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ወጥነትና ወቅታዊ የስራ ደረጃን በሚገልጽ መልኩ የነባሩም የአዳዲስ ፕሮጀክቶች የመረጃ ቋት /Data base/ በማዕከል ደረጃ ሊዘጋጅና ለተጠቃሚዎች የሚደርስበት ስርዓት ሊኖር ይገባል። |
| | 4.17 ኮርፖሬሽኑ ወሰኝ የሆኑ የባለድርሻ አካላትን በመለየት ፕሮጀክቶች ስራቸውን ከመጀመራቸው በፊት የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ መደረግ አለበት። |
| | 4.18 ኮርፖሬሽኑ ወሰኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በተፈራረመው መግባቢያ ሰነድ መሠረት ተግባራዊ መሆኑን መከተታል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። |

**አባሪ 2. የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የአሰራር ሥርዓት ትንተና (Process Description)**



## አባሪ 3. የአዳዲስ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ዕቅድ አፈጻጸም

በአዳዲስ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክቶች ማለትም ጣና-በለስ፣ ኩራዝና ወልቃይት ስኳር ፋብሪካዎች ለመገንባት በተያዘው ዕቅድ መሠረት አፈጻጸማቸው የተጓተተ ሲሆን በዓመቱ በብረታብረትና ኢንጂኒየሪንግ ኮርፖሬሽን በኩል የኮንትራት ውል ተፈጽሞ የተጀመሩት ፋብሪካዎች አፈጻጸም በዓመቱ መጨረሻ እንደሚከተለው ነው፡

| ዝርዝር | ክብደት | % አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በለስ 1 | በለስ 2 | ኩራዝ 1 |
| ዝግጅት | 5% | 5% | 4% | 5% |
| ዲዛይን | 15% | 13.4% | 13.3% | 15% |
| የፋብሪካ ማሺነሪ ማምረት ማቅረብ | 25% | 13% | 12% | 25% |
| የሲቪል ሥራዎች | 25% | 14% | 10% | 25% |
| ተከላ | 25% | | | |
| ፍተሻ | 5% | | | |
| ድምር (አጠቃላይ አፈጻጸም) | 100% | 45% | 39% | 42% |